# ዜና ኢዴኃን

በኢዴኃን የሕዝብ ግንኙነትና የማስታወቂያ ኮሚቴ
በየአስራ አምስት ቀኑ እየተዘጋጀ የሚወጣ የዜና መጽሔት

ቀጽ 1 ቁጥር 3 መጋቢት 1997


## ርእሰ አንቀጽ

### በሚያልፍ ግንቦት የማያልፈው የሕዝብ አንድነት እንዳይሸረሸር

የፖለቲካ ድርጅት ለሚታገልለት ሕዝብ ግልፅ ራዕይ እስካላስጨበጠ፥ ዓላማውንም በግልፅ ይፋ እስካላደረገና ለዚህም የሚጠበቅበትን መስዋዕትነት ለመክፈል ቁርጠኝነቱን በግልፅ ካላሳየ የፖለቲካ ድርጅትነቱ ብቻውን የሚያስገኘው አንዳችም ፋይዳ የለም።
በተለይ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅት ድህነት ከቶውንም የለብንም። ዕድሜ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥርዓት በራሱ አምሳል ከቀረፃቸው "ዴሞክራሲያዊ ድርጅት" ተብዬዎች ጀምሮ ለቁጥር የሚታክት የፖለቲካ ድርጅት ብዛት ታዝበናል።
የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃን) በምንም መልኩ የመደራጀትን ሙሉ መብት የሚያከብርና ለዚህም የሚታገል በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ብዙ ጊዜ አያባክንም። ደጋግሞ የሚነሳው ጥያቄ ግን እንደ ፖለቲካ ድርጅቶቻችን ብዛትና ፍላጎት ኢትዮጵያውያን ካለንበት የመከራ አዘቅት መውጣት ችለናል ወይስ አልቻልንም? የሚለው ጥያቄ ነው። ያለ ጥርጥር መልሱ አሉታዊ ነው።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ትናንትም ሆነ ዛሬ በመከራው ቁስል እንጨት ለሚሰዱበት አጥፊዎች እየታደለ በመከራና በስቃይ አዙሪት ተተብትቦ የፍትኅ ያለህ እያለ የድረሱልኝ ጩኸት በማሰማት ላይ መሆኑን የሚክድ ይኖራል ለማለት ያዳግታል።
እንደሚታወቀው ኢዴኃን ሊመሰረት የቻለው በቅድሚያ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ብለው ራሳቸውን ላደራጁ ኃይሎች የኅብረት ትግል ጥሪ በማድረግ ነበር። በኢትዮጵያ ጉዳይ ራሱ ፈራጅ ራሱ ቀዳጅ ሳይሆን ከሌሎች ጋር አብሮ በጋራ ጥረት የጋራ ጠላትን ለማስወገድ መጣር ኃላፊነት ከሚሰማው ወገን የሚጠበቅ ነውና ከመነሻው ተገቢ ተግባር ተፈፅሟል። ፈረንጆቹ እንደሚሉት ከሁሉ በፊት ችግርን ጠንቅቆ ማወቅ በራሱ መፍትሔ ነውና።
ከኅብረት ጥሪውም በኋላ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ብለው ለተሰባሰቡ ድርጅቶች እንደ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሁሉ የራሱን ቻርተር አስቀድሞ አዘጋጅቶ በቻርተሬ ላይ እንነጋገርና እናፅድቀው አይደለም ያለው-የኢዴኃን መሥራች ጉባዔ። ይልቁንም በኢትዮጵያ ሁኔታና ባለፉ የፖለቲካ ትግል ሂደቶች ላይ ግልፅና ጥልቅ ግምገማ በማድረግ የጋራ ግንዛቤና አቋም በመውሰድ ነው ወደ ኅብረት ምስረታ ስምምነት የተደረሰው። ዛሬም ያልተመለሰው ጥያቄ ታድያ ከኅብረቱ ተሰናብተናል የሚሉና አዲስ

ጎጆ የወጡ ጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች የምሥረታው ወቅት ግንዛቤያቸውና ከሌሎች ለማበር የወሰዷቸው አቋሞች ትክክል አልነበሩምን? የወቅቱ የጋራ ግንዛቤና አቋማቸው ትክክል ከነበረ ከጋራ ጎጆ ወጥቶ ሌላ ጎጆ መቀለስ ለምን አስፈለጋቸው? ራስን ለመቻል ወይስ እኔ በቀደድሁት ቦይ የማይፈስ ሁሉ የኔ አጋር አይደለም ለማለት? የጋራ ጎጆ ሲቀለስ በጋራ ዓላማና ፕሮግራም ታግሎ በጋራ የመንቀሳቀሻ መደላድል ለማመቻቸት ወይስ በጋራ ቤት በግል ፍላጎት እንዳሻው ለመሆን? አዎን ጉዳዩ አያሌ ጥያቄዎችን ያስነሳል::

ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው ግን ኢዴኃኅ በምንም መልኩ ይሁን በምን የመደራጀት ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲጠበቅና ለዚህም አጥብቆ የሚታገል ስለሆነ ማንንም ለምን በዚህ መልክ ተደራጀህ/ሽ ብሎ አይጠይቅም፤ መተክላዊ አቋሙ ነውና ጠንቅቆ ያውቀዋል:: ገና ከጥንስሱ በማናቸውም መልኩ የተደራጁ ኢትዮጵያውያንን ለኅብረት ጥሪ ጋብዞ ግብዣውም የተሳካ ሆኖ ኅብረቱ እውን የሆነውም በዚሁ መንፈስ ነበር::

እንደሚታወሰው ውሎ ሳያድር ኅብረቱ በኅብረትነት ይፋ ሆንሁ ሲል ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው እንዲሉ ኅብረት አይደለም የተመሰረተው የሚሉ ብቅ አሉ:: ከወቅቱ የኅብረቱ አባላት ጥቂቱ የኅብረት ስምምነት ፊርማቸው ሳይደርቅ ሳለመዋሃድ የውኅደት ነጋሪት ጎሰሙ:: የተጎሰመው ነጋሪት ተሰምቶ ሳያበቃም አንዱ ባንዱ ላይ የመፋረስ ክስ በመመስረት ዳኙን በሚል አቤቱታ ሕዝብን ለፍርድ ተማፀኑ:: መፋረስ የተጠናወተው የትግል ሂደትን በቀጣይነት የተያያዙ ክፍሎች ተግባር ኢዴኃኅ ከተመሰረተ ማግስት ጀምሮ የተነሳሳውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ማደብዘዝ ላይ ሆነ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅቶቻችን በአንድ ሊያብሩ ቻሉ እሰየው ብሎ ሳይጨርስ እንደገና በታደሰው የትግል መንፈሱ ላይ ቀዝቃዛ ውኃ ተቸለሰበት:: በዚህም ሃላፊነት የጎደለው ግብዝና ራእየ ቢስ ባህርይ የአቶ መለስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ የሚፈልገውንና አጥብቆ የሠራበትን ጥቂት እፎይታ ገበየ:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል በሁለት ጎራዎች ማለትም በተቃዋሚዎችና በሕወሓት/ኢሕአዴግ መካከል መሆኑ ቀርቶ ዳግም የጓልዮሽ ተሳበ::

ይኸ የኢትዮጵያን የኅብረት ፖለቲካ ታሪክ እንደገና ወደኋላ የጎተተው ክስተት እንዳይወገዝና እኩይ ድርጊቱም እንዲሸሸግ የሌባ ዓይነ ደረቅ እንዲሉ እኒሁ ኃይሎች ኢዴኃኅን እየስነጣጠሩ መተቸትን ወጋቸው አደረጉት:: ሕዝቡን የትግሉ ተሳታፊ የማድረግ አስፈላጊነትን የኅብረቱ መሥራች ጉባዔ ውሳኔ እንዳልሰጠበት ሁሉ በተለይም ኅብረቱ በድጋፍ ኮሚቴዎች መታገዙ÷ የብሔር/ብሔረሰብ ድርጅቶችን ማቀፉና ለሥር-ነቀል ለውጥ መነሳቱ እንደ ኃጢአት ተቆጠሩ::

አንድ የፖለቲካ ድርጅት ለዓላማው መሳካት አባላትን ማፍራትና የትግሉ አጋርና አጋዥ አድርጎ በሰራዊትነት ማሰለፍ ዋናና ቀዳሚ ተግባሩ ነው:: የፖለቲካ ድርጅት አባላት ይመለምላል÷ መብትና ግዴታቸውንም እንዲወጡ ያደርጋል:: አባልነት ፍላጎትን ብቻ ሳይሆን ግዴታንም የግድ ይላል:: የፖለቲካ ድርጅት ከአባላት ባሻገር ደጋፊዎችን ማፍራት ከቻለም እሰየው ወዳጆቹን አበራከተ:: ማንም ግለሰብ ማንንም ድርጅት የመደገፍ ፍላጎቱ የተከበረ ቢሆንም ታድያ ግዴታው አይደለም:: የዛሬዋ ኢትዮጵያችንን ሁኔታ መጋፈጥ ግን የግዴታ እየሆነ መጥቷል - ጤናማ አእምሮ ላለው ዜጋዋ ሁሉ:: እንደ ኢዴኃኅ ላለ የብዙ ፖለቲካ ድርጅቶች ማዕከል ደግሞ ከኅብረቱ አባል የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት በተጨማሪ አጠቃላዩን ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ ማሳተፍ የሚጠበቅበት እንጂ የሚከለከለው መሆን የለበትም:: ደጋፊዎች በራሳቸው አነሳሽነት ትግሉን ሊደግፉ ሲነሱ ደግሞ አቅፎ ደግፎ በትግሉ ማሳተፍ ተገቢ እርምጃ ነው:: ይኸ ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ተግባር የኅብረቱ አባል ለነበሩ ለጥቂቶች እንደ ግዙፍ ችግር ለብዙኃኑ ደግሞ እንደ ብርቱ ክንድ ተቆጥሮ ጎራ አስለይቶ ሲያነታርክ መክረሙ ለተወሰነ ወቅትም ቢሆን እንቆቅልሽ ነበር:: በየትኛውም ጥልቅ ምርምርና ጥናት እውቀት ቢፈተሽ ድጋፍን ማሰባሰብ እንደምን ኃጢአት

ሊሆን እንደሚችል ለብዙዎች ዛሬም ሚስጥር ነው፡፡ የሚገርመው የኢዴፓነን የድጋፍ አካሎች ማቋቋምና በነዚህም አማካኝነት ድጋፍ ማሰባሰብን እንደነውር ያዩትና ይህንንም እንደ አንድ የኅብረቱ ድክመትና ጥፋት ቆጥረው ከኅብረቱ ራሳቸውን ያሰናበቱ ጥቂት ድርጅቶች ሳይውል ሳያድር ለተቃዋሚዎች በሚል በስውር በሰሜን አሜሪካ ልዩ ልዩ ከተሞች ገንዘብ በማሰባሰብ ላይ መሆናቸውን ስንሰማ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ በማለት የተግባራቸውን አግላይነት በፅኑ አወገዝን፡፡ በሚያልፍ ግንቦት የማያልፈውን የሕዝባችንን አንድነት ለመሸርሸር መሞከር የሚያተርፈውን የታሪክ ጠባሳም ልብ ሊሉት እንደሚገባ መከርን፡፡

ኢዴፓኅ በግልም ሆነ በቡድን የተሰባሰቡ ኢትዮጵያውያንን ድጋፍ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም በመርኅ ደረጃ ተቀብሎ ተግባራዊ እያደረገ ሲሆን ያለጥርጥር ያለነዚህ የቁሳቁስ የሃሳብና የንዋይ ድጋፍ ምሰሶዎቹ ዛሬ ካለበት ደረጃ ሊደርስ አይችልም ነበር፡፡ እኒህ የድጋፍ አካሎቹም የምንጊዜም የኅብረቱ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክ ባለውለታዎች መሆናቸውን ኢዴፓኅ በፅኑ ያምናል፡፡

ኢዴፓኅ እንደ ደጋፊዎቹ ሁሉ አባል ድርጅቶቹን የተቀበለውና የሚቀበለው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በማረጋገጥ ብቻ እንጂ በብሔር/ ብሔረሰብ፥ በሙያ ወይም በፆታ መደራጀታቸውን በመጠየቅ አይደለም፡፡ የመደራጀት መብት ከዲሞክራሲና ከዓለም-አቀፍ ሰብአዊ መብቶች አንፃር የሚታይ እንጂ ከልካይና ተከልካይ ያለበት አይደለም፡፡ የመደራጀት መብት የተደራጀው ክፍል ሲሆን የተደራጀበትንም ዓላማ የማሳኪያው ዘዴ የራሱ የተደራጁ ክፍል ነው፡፡ አንድ ራሱን በራሱ ፍላጎትና ፈቃድ ያደራጀ ክፍል ሌሎች የተደራጁበትን ፍላጎትና ፈቃድ ከመጠየቁ በፊት የራሱን ማንነት እንዴትና እንደምን እንደተደራጀ መለስ ብሎ ራሱን የሚመለከትበት አንገት ሊኖረው ካለያም ራሱን የሚያይበትን የቤቱን መስታወት ማፅዳት የቅድሚያ ተግባሩ መሆን አለበት እንጂ የተደራጀውን ክፍል ጠያቂ ራሱን ሿሚ ሽላሚ ማድረግ የለበትም፡፡ የተደራጁ ክፍሎች የተደራጁበት ዓላማና ውጤት ይጠቅመኛል ወይም ይጎዳኛል ብሎ የሚወስነው የተደራጁለት ክፍል ብቻ ነው፡፡ ኢዴፓኅ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ድርጅቶች መዛኙ ብቸኛ ኃይል የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን አጥብቆ ያምናል፡፡ ስለሆነም በፈቃዳቸው የተደራጁ ክፍሎችን የፆታ፥ የሙያ፥ የብሔር/ብሔረሰብ፥ ወዘተ.... ናችሁና ለተደራጃችሁለት ክፍል አትጠቅሙም ብሎ ራሱን አዛዥ ናዛዥ አያደርግም፡፡ ይኽ ዓይነቱ አካሄድ የምንታገልለትን የፍትኅና የዲሞክራሲ ሥርዓት ከወዲሁ የሚፃረር በመሆኑ ይልቁንም ድርጊቱን አጥብቆ ያወግዛል፡፡ የዚህን አመለካከት አራማጆችም ከአንደበታቸውም ሆነ ከከፋፋይ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ይመክራል፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትግል ሂደት እንኳንስ አንድን የፖለቲካ ድርጅት ሌላው ሊፈቅድ ወይም ሊከለክል ይቅርና አንዱ ከሌላው የሚለይበትን መንገድ ጥርጥር ብጥር አድርጎ ለማሳወቅ የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ መድረክ ገና አልተፈጠረም፡፡ ኢዴፓኅ ይኽ ሁኔታ እንዲፈጠር ነው የተቋቋመው፥ ለዚህም እውን መሆን እስከ መጨረሻው በፅናት ይታገላል፡፡

ዛሬ የወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት አንዱን ሕገ-ወጥ ሌላውን ሕጋዊ፥ አንዱን ጠረኛ ሌላውን ሰላማዊ፥ አንዱን የውስጥ ሌላውን የውጭ እያደረገ የተቃዋሚ ኃይሎችን ለመከፋፈል የሚጠቀምበትን ዘዴ በተቃዋሚ ጎራ ያሉትም የራሳቸው መለኪያ እያወጡ የበለጠ የሚሰነጣጥሩት ከሆነ በመካከሉ የሚጎዳው ራሱ የተቃዋሚው ጎራ ብሎም እንታገልልሃለን የምንለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን የሚጠቀመው ደግሞ የሕዝቡ ስቃይና መከራ ተጠያቂ የሆነው የአቶ መለስ ወያኔ/ ኢሕአዴግ ሥርዓት ብቻ ነው፡፡

የአንዲት ኢትዮጵያን ልዕልናና የጠቅላላውን ሕዝቧን ክብርና ነፃነት ዋና ዓላማቸው ያደረጉ ነገር ግን በልዩ ልዩ መልክ የተደራጁ ኃይሎችን ማሰባሰብ ነው-የኢዴፓኅ ቀዳሚ ተግባር፡፡ እኒህ ኃይሎች ተቀራርበ በመሥራት እርስ በርሳቸው እየተዋወቁና እየተማመኑ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት

በሚደረገው ትግል ሂደት አብረው ከቆሙም የሚታገሉለት ሕዝብ ዋና መለያ በሆነው አንድነት ከራሳቸው በሚመነጭ ፍላጎት የማይተሳሰሩበት አንዳችም ምክንያት የለም ብሎ ያምናል- ኢዴኃን::

የኢትዮጵያዊነት መከሰቻው ኅብረ-ብሔራዊነት ብቻ ነው ብሎ ማሰብ የምንታገለውን በሌሎች ላይ የበላይነትን ማንገስ ብቻ ሳይሆን ከኔም በላይ ላሣር ወደሚል ትምክህት እንዳያመራ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል::

ኢትዮጵያ አገራችን የአያሌ ብሔር/ብሔረሰቦች ሙዚየም ናት የምንለውን እምነታችንን በአንደበት ከመናገር ባሻገር በተግባርም የምናውለው መሆን ይኖርበታል:: ኅንጉርጉርነታችን የኢትዮጵያችን ውበት መገለጫ ነው:: ኢትዮጵያዊነት የጠቅላላው ሕዝባችን የአንድነት መቀነት እንጂ የኅንጉርጉርነቱ መሰረዣ ወይም መደበቂያ አይደለም:: ግለሰብ ወይም ድርጅት የአንድ ብሔር / ብሔረሰብ አባልነቱን ወይም መገኛነቱን በጠቀሰ ወይም ባነሳ ቁጥር ኢትዮጵያዊነቱን የሸሸ ወይም የካደ አድርጎ መቁጠር ችኩል ባሕርይ ከመሆኑም በላይ ግለሰቡን ወይም ድርጅቱን ባላደረሰው ጥፋት እንደ መወንጀለኛ መቁጠርም ነው::

ኢትዮጵያዊነት በመወለድ ጭምር የሚወረስ ከኢትዮጵያና ከሕዝቧ የመተሳሰሪያ ጥብቅ ማተብ ነው:: ማተብን ለመበጠስ ወይም ለማስበጠስ መኳተን ከአገርና ከሕዝብ መቆራረጥን ስለሚያስከትል ኢትዮጵያን ከብሔር/ብሔረሰቦቿ ተወላጆች ማቀያየሙን የወያኔ/ኢሕአዴግ ይበቃናል ብለን ለግዙፉ ግባችን ለአገራችንና ለሕዝቧ ነፃነት እንዲሁም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ ብናብር ይጠቅማል::

የወያኔ/ኢሕአዴግን ኋላ-ቀር ሥርዓት አጥብቀን የምንታገለው ሥርዓቱ በፍፁም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የማይበጅ በመሆኑ ነው:: ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ሰንደቅ-ዓላማ ክብርን ከመንፈግ አንስቶ የአገራችንን ድንበር አሳልፎ በመስጠት ብሎም ለሕዝቧ እንግልት እስር ሞትና ስደት ተጠያቂ በመሆኑ በሥር-ነቀል ለውጥ ተወግዶ በምትኩ አዲስ የሽግግር ሥርዓት ብሎም በሕዝብ የተመረጠ ሕዝባዊ አስተዳደር እንዲመሰረት መታገል የወቅቱ ጥሪ ሆኗል::

በፋሲካ የተዳረች ሁሌም ፋሲካ ይመስላታል እንዲሉ ሥር-ነቀል ለውጥን ስንጠይቅ ልጆቹን የበላው የስልሳ ስድስቱ አብዮት ከፊታቸው ድቅን የሚልባቸው አይጠፉም:: አብዮት በግፍ ላይ ማመፅን ለአምባገነኖች እምቢኝ ማለትን እንጂ ከደም ጎርፍ ጋር የባሕርይ ግንኙነት የለውም:: ትግላችን የወያኔ/ኢሕአዴግን አስከፊ ሥርዓት ከሥሩ መንግለን ጥለን በምትኩ ሕዝባዊ ሥርዓትን ለመትከል ነው:: ሕዝባችንን ከመከራና ከስቃይ ለማዳን እንጂ ዳግም ወደ ደም ጎርፍ ላለመመለስ መወሰናችችንማ ሀ ሲባል የሰላማዊ የትግል ስልትን በመቀበል አረጋግጠናል:: ለዚህም ማስረጃ የሚጠይቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ ሌላ ማንም ኃይል ሊኖር እንደማይችል ደግመን ደጋግመን ልናረጋግጥ እንወዳለን::

የወያኔ/ኢሕአዴግን ሥርዓት ራሱ ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠረው የምርጫ ቦርድና የምርጫ ሥርዓት ተሳትፎ ማስወገድ ይቻላል ለሚሉ ተቃዋሚዎች ደግመን ደጋግመን ሂደቱ አጃቢነት እንዳይሆንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ምኞትና ፍላጎት በሚፃረር መልኩ እንዳይደመደም በቅድሚያ መሟላት ያለባቸውን ጉዳዮች በጋራና በአንድነት ሆነን አምባገነኑ አስተዳደር እንዲያሟላቸው እናስገድድ ብለን አሳስበናል:: ይኸው ጥሪያችን የትናንት ብቻ ሳይሆን የዛሬም የወደፊትም ነው::

ዓላማችን ፍፁም አምባገነን ከሆነ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገር እንጂ ፓርቲን በፓርቲ መተካትም አይደለም:: ፓርቲን ከፓርቲ የምናወዳድርበት፤ ሕዝባችን አምባገነኑ ሥርዓት በፈጠረበት ጫና ማጎንበሱን ትቶ አንገቱን ቀና አድርጎ የሚያይበት፤ ኢትዮጵያውያን አምባገነኑ ሥርዓት ካተረፈላቸው መቃቃር ይቅር ተባብለው እጅ ለእጅ ተያይዘው የወደፊቱን የሚመለከቱበት፤ ዳግም በአንድ አገርና በአንድ ሰንደቅ-ዓላማ ጥላ ሥር እንደ አንድ ዜጋ ተማምነን ወደፊት ለመጓዝ የምንችልበትን ድልዳል የምናመቻችበትን

የሽግግር መንግስት አቋቁመንና የሽግግር ሂደትን ተከትለን የተመቻቸ ሁኔታን በመፍጠር በቀጣይ ሂደት ፓርቲን ከፓርቲ ማወዳደሩ ይከተላል በማለታችንም መንግስት እያለ የሽግግር መንግስት አይመሰረትም በማለት የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ የማጣጣል ብሎም በሥልጣን ላይ ላለው መንግስት ይሁንታን የሚሰጥ ትርጓሜ መስማትን የሰርክ ካደረግነው ሰንብተናል።

ይኽ የተሳሳተ ትርጓሜም መሰረቱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመጪው ምርጫ ተሳትፈን የምርጫ ወንበሮች በየ አምስት ዓመቱ እያጠራቀምን የወያኔ/ኢሕአዴግን ሥርዓት ማስወገድ ይቻላል ከሚል የፖለቲካ አቋም ጋር እጅጉን ይዛመዳል። ታዲያ ይኽ በሚነገርበት አፍ ደግሞ በዚህ ምርጫ ሥልጣን ላይ ያለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ካልተለወጠ አገር የመጥፋት አደጋ ላይ ነች ይሉናል። ይኽ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እንዲቆይ ከተፈቀደ ኢትዮጵያም እንደ አገር ኢትዮጵያውያንም እንደ ሕዝብ መቀጠል የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ የሚለው ግምገማና ተሃስቦማ የኅብረቱ መሥራች ጉባዔ የደረሰበትና በጋራ መሥራት አለብን ለሚለው የሙሉ በሙሉ ውሳኔአችን አንዱ የስምምነት ነጥባችን ነበር። ታዲያ አሁን የሚስተጋባው ዘመቻ ተቃርኖ ያለውና የማይጣጣም ነውኮ! አንድም ሁኔታዎች ተቀይረዋልና አገዛዙ በሥልጣን መቆየቱ በአገራቷና በሕዝቧ ላይ ችግር አያስከትልም ስለሆነም የፈጀውን ያህል የአምስት ዓመቶች ጊዜ ይፍጅ ሁኔታዎች ባሉበት እንደሆኑ አንድ ቀን ዘንቦ ተባርቆ በፓርላማ (በሁለቱም ምክር ቤቶችና በየክልል ምክር ቤቶች) አብዛኛውን መቀመጫ በማግኘት ለውጥ ማምጣት ይቻላል ነው፤ አለያም ኢትዮጵያም ኢትዮጵያውያንም አደጋ ላይ አደሉም፥ ወደተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገርም ሆነ ለፈርጀ ብዙና መጠነ-ሰፊ ችግሮቻቸው አፋጣኝ ምላሽ አያስፈልጋቸውም ነው? የትኛው ነው?

ደጋግመን እንደገለጥነው ሁሉም ነገር በወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት ብቸኛ መዳፍ ሥር በወደቀበት ሁኔታና ይኸው ሥርዓት ብቻ ሁሉንም ፈቃጅና አዛዥ በሆነበት ባሁኑ ወቅት ፍትኃዊና ርትአዊ የሆነ ምርጫ ሊካሄድ ስለማይችል በገለልተኛ አካል እንዲፈፀም አሳስበናል። በስልጣን ላይ ካለው ገዥ ፓርቲ ጋርም እስከዛሬ ድረስ በድርድር ላይ እንገኛለን። ለዚህም ተፈፃሚነት በአንድ እንድንቆም በተቃዋሚነት ተሰልፌያለሁ ለሚሉ ሁሉ የጋራ ትግል ጥሪ አቅርበናል። እስካሁን ግን የተጨበጠ ምላሽ አላገኘንም። ከዚህ በኋላ ጉዳዩ የሁላችንም ፈራጅ በሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ ነው ብለን እናምናለን።

እጅጉን የሚገርመውና የሚደንቀው የሰሞኑ አዲስ ክስተት ደግሞ የኅብረቱን አቋሞች እያንሻፈፈ የሚተረጉመው የወያኔ/ኢሕአዴግ አዲስ ፀረ ኢዴኃኅ ቅስቀሳ ነው። ሰሞኑን በአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ያደርጓቸዋል በሚባሉ ክርክሮች ላይ አገዛዙን ወክለው የቀረቡት የሥርዓቱ የማስታወቂያ ሚኒስትር ኢዴኃኅ ምርጫውን ያጣጥላል፤ ምርጫውን ሊያደናቅፍ ይጥራል፤ አመፅም ለማስነሳት አቅዷል ሲሉ ከመክሰሳቸውም በላይ በተከታታይ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ይኸው የአገዛዙ አቋም ሆን ተብሎ ተደጋግሞ እየተንፀባረቀ ነው። ጉዳዩ አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ ዓይነት ነው። ኢዴኃኅ ትናንትም ሆነ ዛሬ አቋሙ አንድና አንድ ብቻ ነው። ዛሬ በኢትዮጵያችን ላይ በጠመንጃ አፈሙዝ ስልጣን የተቆናጠጠው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የማይበጅና መወገድ ያለበት ሥርዓት ነው፥ አራት ነጥብ።

ይኽ አገዛዝ ሁሉንም ጉዳይ በራሱ ብቸኛ ቁጥጥር ሥር አድርጎ ባሻው የሚፈነጭ አምባገነን ሥርዓት መሆኑን በፅኑ ብናምንም መከራና ስቃይ ሲፈራረቁበት የኖረው ሕዝባችን ዳግም በደም ዘመን ማለፍ የለበትምና በሰላማዊ የትግል ስልት እንዲወገድ ለማድረግ ድርድር ውስጥ ጭምር ገብተናል። የድርድር ነጥቦቻችንንም የማስፈፀም ሙሉ መብትና ኃይል ላለው ሕዝባችን ይፋ አድርገናል። ለድርድር ያቀረብናቸው ወሳኝና ዓቢይ ጉዳዮች እስኪፈፀሙ ድረስ እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ ስለሌለብን እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ በሙሉ ልብ

ድርጅቶች በሚገኙባቸው የአውሮጳ አገሮች የድጋፍ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም የሚደረገው ጥረት እንደቀጠለ መሆኑን የደረሰን መረጃ ጨምሮ ገልጿል።

## የኢዴኃኅ አጪዎችን የመሰረዝና የማዋከብ ድርጊት እየተፈፀመ መሆኑ ታወቀ።

ኢዴኃኅ ለመጪው ግንቦት ምርጫ በምሥራቅ ጎጃም ሞጣና በትግራይ አዲጉደን ወረዳዎች ያቀረባቸው እጩዎች ባልታወቀ ምክንያት በወያኔ/ኢሕአዴግ የምርጫ ቦርድ እንዲሰረዙ መሆኑን ከአካባቢው የደረሱን መረጃዎች አረጋገጡ።

ጉዳዩ የምርጫ አስፈፃሚዎች የምርጫ ሕጉና ቦርዱ በአንድ ገዢ ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በሆነበት ሁኔታ ሊፈፀም መቻሉ ባያስገርምም ኅብረቱ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየተንቀሳቀሰ ያደረጋቸው ጉልህ ተግባራት ያስደነገጠው የወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት በተከታታይ ወደፊትም ለሚያደርሳቸው ግድፈቶች ምንም ዋስትና እንደሌለ የእጩዎች ስረዛው በቂ ምስክር መሆኑን ለመገመት አያዳግትም።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የደረሰን ዜና እንዳመለከተው በውክልና በየወረዳዎቹ መመዝገብና መወዳደር እንደሚቻል የሚደነግገውን የራሱን ሕግ በመሻር የወያኔ/ኢሕአዴጉ የምርጫ ቦርድ በመርጦላ ማርያም አካባቢ ለመወዳደር ያመለከቱትንም እጩ ጉዳይ እስካሁን እልባት ባለመስጠት ሆን ብሎ እያጓተተ መሆኑንም የደረሱን ዘገባዎች አረጋግጠዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር በሚገኙባቸው በተለይ እንደ የኦሮሞ ክልል ባሉ ክፍሎች እጩዎች ላይ የመዛት፥ እንዳይወዳደሩ የማስፈራራት እንዲሁም ከምርጫው ራሳቸውን እንዲያገሉ ግፊት የማድረግ ወከባ እየደረሰም መሆኑ ታውቋል።

ኢዴኃኅ የተጠቀሱትን ዓይነት ተከታታይ ጥቃቶች ቢፈፀሙበትም በጠቅላላ አገሪቱ ጎላ ያለ ቁጥር ያለው እጩ በማስመዝገብ፥ በተለያዩ ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባዎች በማድረግና ከሌሎች ተቃዋሚዎችና ከመንግስት ተወካዮች ጋር በሚደረጉ ክርክሮች በመሳተፍ ትግሉን እያፋፋመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

## በሰሜን ጎንደር በተደረገው ስብሰባ ኢዴኃኅና የመንግስት ተወካዮች ብቻ ተከራከሩ ።

የካቲት 27 1997 ዓ. ም. የኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር በጠራውና በጎንደር ሲኒማ አዳራሽ በተከናወነው ስብሰባ ላይ የኢዴኃኅና የወያኔ/ኢሕአዴግ ተወካዮች ብቻ ክርክር ማድረጋቸው ሲታወቅ "ቅንጅት ለዲሞክራሲና ለፍትኅ" የተሰኘው ክፍል ስብሰባው በወያኔ ኢሕአዴግ የተዘጋጀ ነው በሚል ስብሰባውን ረግጦ መውጣቱን የደረሰን ዜና አስረድቷል።

በስብሰባው ላይ የኢዴኃኅ ተወካዮች በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በ'አገሪቱ ላይ ስላደረሰው በደል በሕዝብ ፊት በዝርዝር ለማስረዳት ከመቻላቸውም በላይ በቀጣዩም ምርጫ በራሱ የምርጫ ቦርድ በመታገዝ አሸንፍኩ ለማለት ካሁኑ የሚያዘጋጃቸውን የማጭበርበሪያ ስልቶች በመረጃ አጋልጠዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የኢዴኃኅ ተወካዮች መጋቢት 4 1997 ዓ. ም. በመተማ ከተማ ለሚደረግ ስብሰባ ወደአካባቢው ተጉዘው ከነዋሪው ጋር ሰፊ ውይይት እንዳደረጉ የደረሰን ዜና ጨምሮ ገልጿል። ይኸ የመተማ ደማቅ ስብሰባ ኢዴኃኅ በጣም በውስን አቅሙ የድንበር አካባቢዎችን ጭምር ለማዳረስ የሚያደርጋቸውን ብርቱ ጥረቶች አመላካች እንደሆነ ታዛቢዎች ጠቁመዋል።

## የኢዴኃኅ የአካባቢ ውይይቶች በውጭውም ዓለም እየተካሄዱ ነው።

ኢዴኃኅ እንደ አገር ቤቱ ሁሉ በውጭውም ዓለም የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ አባላት በሚገኙባቸው ከተሞች ስለ ኅብረቱ የወደፊት አቅጣጫና ስለተያዙት እቅዶች በተለይም ስለመጪው ምርጫ ተከታታይ ገለጻዎችን ለማድረግ ባቀደው

መሰረት ሁለተኛውና ሦስተኛው ስብሰባዎች የካቲት 16 እና መጋቢት 6 2005 ዓ/ም እ. አ. አ. በዋሽንግተን ዲሲ መከናወኑ ተገለፀ።
ስብሰባዎቹ እንደቀዳሚዎቹ ሁሉ በዋሽንግተን ዲሲ 16ኛው መንገድ ላይ በሚገኘው ዩኒፊኬሽን ቸርች አዳራሽ ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 9 ሰዓት (3 PM) ጀምሮ የተካሄዱ መሆኑ ሲታወቅ አቶ ፋሲካ በለጠ የኢዴኃኅ ምክትል ሊቀመንበርና መቶ አለቃ አያል ሰው ደሴ ምክትል ፀሓፊው ተገኝተው ሰፊ ዘገባና መግለጫ አቅርበዋል።
ይኸው ውይይት በቀጣይነት በየአስራ አምስት ቀኑ በዲሲና በሌሎችም ከተሞች እንደሚከናወን ከአዘጋጁ ከኢዴኃኅ የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ቢሮ የተገኘው ዜና ጨምሮ አብራርቷል።

## የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴዎች ያዘጋጁቸው ስብሰባዎች በደመቀ ሁኔታ ተጠናቀቁ።

የካቲት 2005 እ. አ. አ. በሰሜን አሜሪካ በሎስ አንጀለስ ከተማ የኢዴኃኅ የአካባቢው የድጋፍ ኮሚቴ ያዘጋጀው ስብሰባ በከፍተኛ ድምቀት መከናወኑን የደረሰን ዜና አረጋግጧል፤
በዚህ ስብሰባ ከኢዴኃኅ የኀብረቱ ምክትል ው/ፀሓፊ የመቶ አለቃ አያል ሰው ደሴ የተገኙ ሲሆን ስለ ኀብረቱ የወቅቱ እንቅስቃሴዎች ስለ ወደፊት እቅዶችና በተለይም በወቅቱ አንገብጋቢ ዋነኛ የገንዘብ አቅም ጉዳይ ሰፊ ማብራሪያ መስጠታቸው ታውቋል።
በዚሁ ስብሰባ የአንጋፋው የኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት የተገኙ ሲሆን በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ገለፃ ማድረጋቸውንም ከአካባቢው የደረሰን ዜና ጨምሮ ገልጧል።
በተመሳሳይ ሁኔታ በሴንት ሉዊስ የኢዴኃኅ የድጋፍ ኮሚቴ የተጠራው ስብሰባም ቅዳሜ መጋቢት 12 2005 የተከናወነ ሲሆን በዚሁም ስብሰባ ላይ የወቅቱ የኢዴኃኅ ምክትል ዋ/ፀሓፊ መቶ አለቃ አያል ሰው ደሴ ተገኝተው ስለወቅቱ የኀብረቱ እንቅስቃሴ ሰፊ መግለጫ ሰጥተዋል።
ስብሰባው የአድዋን ድል 109 ዓመት መታሰቢያ ያከበረና ደማቅና ተተሳካ እንደነበር ተገልጿል።

## የወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት ለተቃዋሚዎች የሚደረጉ ድጋፎችን ለራሱ እንደሚያደርግ ተገለፀ።

የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግስት እራሱ በፓርቲዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የደነገገውንና መንግስት በአገሪቱ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ ይሰጣል የሚለውን ሕጉን እስካሁን ተግባራዊ ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ከውጭ የሚመጡትንና ለሁሉም ፓርቲዎች ድጋፍ እንዲሆን የሚገኘውን እርዳታ ሁሉ ለራሱ በማስቀረቱ ለጋሽ አገሮች የእርዳታ አሰጣጣቸውን ዘዴ እንዲቀይሩ መገደዳቸውን ከአገር ውስጥ የደረሱን ዜናዎች አረጋገጡ።
በዚሁ መሰረት ከዚህ በፊት ለፓርቲዎች በአጩዎቻቸው መጠን ጥቂት የገንዘብ ድጎማ የሚያደርጉ ለጋሽ አገሮች ካሁን በኋላ በገንዘብ ሳይሆን በቁሳቁስ መልክ ብቻ እርዳታ ለማድረግ በመወሰናቸው ልዩ ልዩ ጥሬ ገንዘብ ለሚጠይቁና ለፖለቲካ ድርጅቶች የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመሸፈን አለመቻሉን በአገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አቤቱታዎች እየጠቆሙ መሆኑንም ከስፍራው የደረሱን ዜናዎች ጨምረው ገልፀዋል። በተለይም በተቃዋሚ ጎራ ያሉቱ በዚህ ረገድ ያለባቸው የገንዘብ አቅም በውጭ በሚኖሩ ዜጎች ድጎማ ላይ ብቻ እንዲወሰኑ እንዳደረጋቸውም የደረሰን ዜና አክሎ ገልጿል።

## የወቀቱ የኢዴኃኅ ሊቀ-መንበር በውጭ የሥራ ጉብኝት አደረጉ።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሊቀ መንበር ዶ/ መረራ ጉዲና ለስብሰባ ወደ አውሮጳ ዘልቀው እንደነበር ታወቀ። ሊቀ መንበሩ በሰሜን አሜሪካ አጭር የሥራ ጉብኝት ማድረጋቸው ተገልጿል። በዚህ

አጭር ጊዜ ጉብኝት በሰሜን አሜሪካ ከሚገኙ የኅብረቱ የአመራር አባላት ጋር በመሆን በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት (ስቴት ዲፓርትመንትና) እና በአሜሪካ ኮንግረስ ከሃላፊዎች ጋር ጠቃሚ ውይይቶችን ማድረጋቸው፥ በዋሽንግቶን ዲ.ሲ.እና በካሊፎርኒያ ቤይ ሰላጤ አካባቢ ከሚገኙ የኅብረቱ ደጋፊዎችና ተባባሪዎች ጋር ሰፊ ውይይቶችና የሃሳብ ልውውጦች ማድረጋቸውን እንዲሁም የደቡብ ኢትዮጵያ ሕ.ዴሞ. ኅብረቱ በማርች 12 2005 (እ.አ.አ.) በዋሽንግቶን ዲ.ሲ. በተዘጋጀው ደማቅ የባሕልና የእርዳታ አስተዋጽዖ ምሽት ላይ ተገኝተው መልእክት ማስተላለፋቸው ከቃል አቀባያችን የተገኘው መረጃ አስረድቷል።

## ኅብረቱ የኢደኃኅን የገንዘብ ችግር ለመቀረፍ የሚያስችል አስቸኳይ ስብሰባ ተካሄደ።

### የድጋፍ ኮሚቴዎችም ወሳኝ ሚና ለመጫወት ወሰኑ።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴዎች መጋቢት 13፣ 2005 እ. አ. አ. ባደረጉት መደበኛ ስብሰባ ኢዴኃኅ ባለበት ወቅታዊ የገንዘብ ችግር ላይ በሰፊው በመወያየት አዲስ የገንዘብ አሰባሰብ እቅድ ማውጣታቸውን በስብሰባው የተሳተፈው የዜና ኢዴኃኅ ቃል አቀባይ አስታወቀ።

የዕለቱን ስብሰባ ልዩ ያደረገው የወቅቱ የኢዴኃኅ ሊቀመንበር ዶክተር መረራ ጉዲና በስብሰባው ላይ ተገኝተው ስለወቅቱ የኅብረቱ እንቅስቃሴ በሰፊው ማብራራታቸውና በተለይ ባሁኑ ወቅት እጅግ ወሳኝ ስለሆነው የኢዴኃኅ የገንዘብና የቁሳቁስ አቅም ዝርዝር መግለጫ መስጠታቸው ሲሆን የሰሜን አሜሪካው ቅርንጫፍ ሊቀመንበር አቶ ፋሲካ በለጠና ምክትል ፀሓፊው መቶ አለቃ አያልሰው ደሴም በበኩላቸው ተጨማሪ ማብራሪያዎችን አክለዋል።

ዶክተር መረራ በተለይ በመጪው ምርጫ ኢዴኃኅ በአሸናፊነት ይወጣ ዘንድና የሚጠበቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት እንዲረጋገጥ የዜግነት ግዴታዬን እወጣለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ የሚገመትበት ወሳኝ ወቅት ላይ ስለደረስን ነገ ሳይሆን ዛሬ ነው ስንቅ ማቀበያው ጊዜ ብለዋል።

ኢዴኃኅ ባሁኑ ወቅት በአገር ቤት ከወጠናቸው ውጥኖች ዋና ዋናዎቹ፥

- የምርጫ እጩዎች በየቦታው እየተዘዋወሩ ራሳቸውንና የኢዴኃኅን አማራጭ ፕሮግራም በሰፊው እንዲያስተዋውቁ ማስቻል፥
- ወሳኝ ወረዳዎችና ከተሞች ላይ የተጀመረው ሕዝባዊ ስብሰባ እንዲቀጥል ማድረግ፥
- በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ላይ የኢዴኃኅን ታዛቢዎች ማሰማራት፥
- በመኪኖች በመታገዝ በራሪ ወረቀቶች፥ ፖስተሮችና ልዩ ልዩ የቅስቀሳ መሳሪያዎች በመጠቀም ሕዝቡን ለምርጫው ማዘጋጀት፥
- የሕዝቡ አስቸኳይ ጥያቄዎች የሆኑትን የአካባቢ ጽሕፈት ቤቶች መክፈት እንዲሁም ቢያንስ ጥቂት ሰራተኞች በየጽሕፈት ቤቶቹ መቅጠርና ማሰራት፥
- በተለይ ሕዝቡን ላለውም ሆነ ለቀጣዩ ትግል በበቂ ለመያዝ ለማደራጀት ከቦታ ቦታ ለሚዘዋወሩ ሰራተኞች የውሎ አበል የመጓጓዣና ሌሎችም ወጪዎች መሸፈን መቻል፥

መሆናቸው በስብሰባው ተብራርቷል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች አንገብጋቢነት የተረዱት የኢዴኃኅ የድጋፍ ኮሚቴ አባላትም ጊዜ ሳይሰጡ ከራሳቸው በመጀመር ኢዴኃኅ ለምርጫው ያዘጋጃቸውን እጩዎች ስፖንሰር የማድረግ እቅድ አውጥተው በዚሁ እቅድ ላይ ለመረባረብ ወስነዋል።

በዚሁ መሰረት ለአንድ እጩ $250.00 ዶላር በአማካኝ ለማዋጣት የሚቻልበት መንገድ እንዲፈለግ ከመስማማታቸውም በላይ በዕለቱ ከተሰበሰቡት የድጋፍ ኮሚቴ አባላት በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን መሰረት ለሰማንያ ስድስት እጩዎች

የሚሆን ገንዘብ ለመዋጣትና ይህንኑ በአስቸኳይ ወደ አገር ቤት ለመላክ ወስነዋል::

የድጋፍ ኮሚቴ አባላቱ ቀርጠኝነት ምን ያህልነት በታየበት በዚህ ስብሰባ ሊሰበሰብ የተገባው ቃል እጅግ አስደሳች ቢሆንም ኢዴኃኅ በእጩነት ያቀረባቸው ተወዳዳሪዎች ከአንድ ሺህ በላይ በመሆናቸው ለእነዚህ ተወዳዳሪዎች ወጪ የሚውለውን ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሰባሰብ እንዲቻል በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በስፖንሰርነት እንዲሳተፉ ወገናዊ ጥሪ በልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎች እንዲተላለፍና ለተግባራዊነቱም ማናቸውም ኢትዮጵያዊ እንዲነሳሳ የአገር አድን ጥሪ አስተላልፈዋል::

በሌላ በኩል እጩዎችን ስፖንሰር ለሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን የእጩዎቹን ማንነት የሚገልፁ አጫጭር ማብራሪያዎችና መግለጫዎች እንደሚሰጡና ረጂዎቹም ይህንኑ የሚያገኙበት መንገድ በአገር ቤት የተቋቋመው የተመራጮች ቅስቀሳ÷ ምልመላ÷ አደራጅና አሰማሪ ኮሚሽን አማካይነት የተዘጋጀ መሆኑም ተገልጿል:: ከዚህ ጉልህ የእጩዎች የገንዘብ ማሰባሰብ እቅድ በተጨማሪ ለሌሎች የኢዴኃኅ ወጪዎች መሸፈኛ የሚሆን ገንዘብ ማሰባሰቡ የሚቀጥል መሆኑና በተለያዩ የኢዴኃኅ የድጋፍ ኮሚቴዎች ባሉባቸው ከተሞች ከዚህ በፊት ይደረጉ የነበሩ የአስተዋፅኦ ምሽቶችና ዝግጅቶች የሚቀጥሉ መሆኑንም የድጋፍ ኮሚቴዎቹ በስብሰባው መግለጣቸውን በስብሰባ የተገኘው ቃል አቀባያችን ጨምሮ ገልጧል::

## <u>ታላቅ የገንዘብ አስተዋፅኦ ዝግጅት-በዋሽንግቶን ዲ. ሲ.</u>

ይድረስ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ

በቅድሚያ የከበረ ወገናዊ ሰላምታችን ይድረሳችሁ::

ውድ አገራችን ኢትዮጵያን ከምትገኝበት እጅግ አሳፋሪና ዘግናኝ ሁኔታ ለማውጣትና ብሔራዊ ክብሯን አግኝታ ለቀጣይ ችግርና ሰቆቃ የተዳረገ ሕዝቧም የሚፈቅደው መንግሥትና አስተዳደር ባለቤት እንዲሆን የሚደረገው ትግል በተበተነ መልኩ እንዳይቀጥል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ምኞትና ግፊት መሆኑ የታወቀ ነው::

የኢትዮጵያ ለውጥ ፈላጊ ኃይሎችም ውስጣቸውን በመመርመርና ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ከየግል የተናጠል የትግል ቅኝታቸው ይልቅ የጋራ የሆነውን የአገርና የሕዝብ ጉዳይ በማስቀደም በ1995 ዓ/ም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች (ኢዴኃኅ)ን በመመሥረት "ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ" ለሚለው የወገናችን የምሬት መልእክት ምላሽ መስጠታቸው በደስታ የሚዘከር ነው::

ኢዴኃኅ በተመሠረተበት መንፈስ ለአገራዊ ዓላማው መሳካት የሚከተለው የሰላማዊ ትግል አካል የሆነው ነፃና ርቱዕ ምርጫ እውን እንዲሆን በመታገል ላይ ይገኛል:: ኅብረቱ በአሁኑ ጊዜ ያቀፉቸውን አሥራ አራት የፖለቲካ ድርጅቶች በመያዝ በኅብረት ደረጃ ሕጋዊ እውቅና አግኝቶ በመጭው ግንቦት 1997 ዓ/ም በአገራችን ሊደረግ በታሰበው ጠቅላላ ምርጫ ሂደት ለመሳተፍ ብሎም በአሸናፊነት ለመውጣትና የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት የሚያደርግ ሥርዓትን ለማስገኘት የሚያስችል ሁኔታን ለማመቻቸት እየታገለ ነው:: ለዚሁ ብሔራዊ ትግል በውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ቀጥተኛ ተሳትፎና ትብብር እንዲያደርግልን የዘወትር ጉትጎታችንና ተስፋችን ነው::

በመሆኑም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በአገራችን በሚካሄደው ምርጫ ለሚያደርገው ትንቅንቅ የወገኖቹ ትብብርና እርዳታ ስለሚያስፈልገው በዋሽንግቶን ዲሲ 2660 Woodly Road ላይ በሚገኘው Marriott Wardman Park ሆቴል ውስጥ April 2, 2005 የገንዘብ መዋጮ ምሽት ያዘጋጀ ሲሆን እርስዎም በቦታው በመገኘት ወገናዊ ትብብርዎን እንዲያደርጉልን ከወዲሁ ስንጠይቅ በታላቅ መተማመንና በከፍተኛ ወገናዊ አክብሮት ነው:: ለአስተዋፅኦው ምሽት የተዘጋጀው ትኬት በኢትዮጵያውያን መደብሮች ሁሉ

**ስለሚገኝ አስቀድማችሁ በመግዛት እንድትተባበሩንም ከአደራ ጭምር በአክብሮት እንጠይቃለን።**
**በመላው አለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንም ቼክ ወይም መኒ ኦርደር ለምትልኩልን አድራሻችን ፥**
***UEDF***
***P. O. Box 73246***
***Washington DC 20056***
**ሲሆን የባንክ አካውንት ቁጥራችን ደግሞ፥**
***Chavy Chase Bank***
***0044378793***
**መሆኑን እንገልፃለን።**

# ከኢዴኃኅ ማኅደር

በዚህ አምድ ላይ ቀደም ሲል ኅብረቱ የወሰዳቸውን አቋሞችና መተከላዊ እምነቶቹን ከማህደሮቹ እየፈተሽን እንዳሉ አቀርበናል። እስከቀርብ ጊዜ ድረስ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግስት ለአንዳንድ ደጋፊ ለሆኑት ኃያላን መንግስታት ጭምር ተቃዋሚዎች አማራጭ ፕሮግራም እንኳ የላቸውም እያለ እንደሚከስ ተደጋግሞ ይሰማል። እንደኢዴኃኅ ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ደግሞ የለም ከመንግስት ነኝ በዩ የተሻለ አማራጭ አለን በማለት ተከራክረዋል። በዛሬው እትም በጥቂት ቀናት ውስጥ የኢደኃኅ አጨዋች ለሚመርጣቸው ሕዝብ የሚያቀርቡትና ከሕዝባቸው ጋር የሚወያዩበት ፕሮግራም ይቀርባል። የአማራጭ ፕሮግራሙን ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች በተከታታይ ከማቀረባችን በፊት ለዛሬ መግቢያውን ብቻ እነሆ።

## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች የቀረበ የጋራ ትግል አማራጭ ሰነድ፤

እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ኃይሎች፡-

. ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታም በማታውቀው ሁኔታ ህልውናዋንና የሕዝባችንን ሰላምና ደህነንት የሚፈታተኑ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊ፥ የአካባቢ ውድመትና ሌሎች ከባድ ቀውሶች ውስጥ መሆኗን በመገንዘብ፤

. እነዚህ ቀውሶች ለዘመናት እየተጠራቀሙ የመጡ መሆናቸው ባይካድም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት አንዳንዴም በቸልተኛነት ሌላ ጊዜ ደግሞ ሆን ብሎ በሚከተላቸው የተሳሳቱ ፖሊሲዎች የተነሣ አስደንጋጭ በሆነና ከዕለት ዕለት መመለሻ በሌለው ሁኔታ እየከፋና እየተባባሱ በመሄድ ላይ መሆናቸውን በማጤን፤

. አስቸኳይ የፖሊሲና የአቅጣጫ ለውጦች ካልተደረጉ ተጨማሪ ቀውሶች እየተፈለፈሉ አገራችን ከፍተኛ ፈተና ላይ ልትውድቅ የምትችልበት አደገኛ ሁኔታ መኖሩን በከፍተኛ ጭንቀት በመገንዘብ፤

. ዛሬ ሀገራችንና ሕዝባችን የተያያዙትን የአዘቅት ጉዞ ባስቸኳይ ገትቶ ማቆምና የገቡበትን የጥፋት አዙሪት መስበር የዚህ ወይም የዚያ ግለሰብ፥ ድርጅት ወይም ስብስብ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ የሆነ፥ ብሔራዊ፥ ሰብዓዊና የሞራል ግዴታና የትውልድ ተልዕኮ መሆኑን በመረዳት፤

. እነዚህን ቀውሶች ለመቋቋምና አጥፊውን ሂደት ለመቀልበስ የሚቻለው በሉዓላዊት አገሩ ሉዓላዊ የሆነ ሕዝብ መክሮና ዘክሮ መፍትሔ ለመሻት የሚችልበት ዴሞክራሲያዊ መድረክ ሲመቻችለት ብቻ በመሆኑ፥ ዛሬ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊና አገር ወዳድ ኃይሎች ተቀዳሚ ተግባር በጋራ ሰላማዊና ሕዝባዊ ትግል ይህንን መድረክ የነፈገውን መንግሥትና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት አስወግዶ በሱ ቦታ በዴሞክራሲዊ ሥርዓት ክልል ውስጥ ጥረቱን የሚያግዝና የሚያስተባብር በሕዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግሥት መመሥረት መሆኑን በመገንዘብ፤

. እዚህ ደረጃ ለመድረስ ለሕዝቡ ትግል ቅንብርና አቅጣጫ የሚሰጥ ግልጽ የሆነ አማራጭ ሰነድና የተደራጀ ኃይል አስፈላጊ መሆኑን በማመንና፥ ይህ እስከሌለ ድረስ ሕዝባችን በግብታዊነት ተራ በተራ እየተነሣ ተራ በተራ እየተመታ የሚሄድበት ወይም ደግሞ ባልሆነ አቅጣጫና ባልሆነ ዘዴ እንዲታገል ለሚገፋፉት የተለያዩ ኃይሎች ሰለባ የሚሆንበት ሁኔታ እንዳለ በሥጋት በማጤን፤

. የአገራችንን ህልውናና የሕዝባችንን ሰላምና ደህንነት በተመለከተ ከፖለቲካ፥ ከብሔር፥ ከርዕዮተ-ዓለም ልዩነቶች ባሻገር፥ ሁላችንም የምንቀበለውና በጋራ ልንዋደቅለት የሚገባን

የጋራ አገራዊ ርዕይ እንዳለን በመገንዘባችንና ይህንንም ለሕዝባችን በማካፈል ሁሉም ለዚህ ዓላማ በጋራ እንዲታገል ማነሣሣት የትውልድ አደራ ነው ብለን በማመን፤

. ዴሞክራትና አገር ወዳድ ነን የሚሉ ኃይሎች በሙሉ ለዚህ ዓላማ በቁርጠኝነት ከቆሙ÷ ሀገራችንና ሕዝባችን የገቡበትን አስከፊ አዙሪት ለመስበር የሚያስችሉ በርካታና ወሳኝ አገር አድን አማራጮች እንዳሉና በነዚህ ላይ ተስማምተው በጋራ ለመታገል የማይነሱበት ምንም ምክንያት አይኖርም ከሚል ፅኑ እምነት በመነሣት፤

. በነሐሴ ወር 1996 ዓ.ም. በሮክቪል ሜሪላንድ ዩ ኤስ ኤ የኢድኃኅ ብሔራዊ ሸንጎ አስቸኳይ ጉባኤ ካፀደቀው የጋራ ራዕያችንን ያካተተ መለስተኛ ፕሮግራም በተጨማሪ የመንግሥት ሥልጣን በመያዝም ሆነ ከዚያ በመለስ ባለው የትግል ወቅት ሕዝባችን የሚገኝበትን አጥፊ አዙሪት ለመስበር እነዚህን አማራጭ የፖሊሲ÷ የአቅጣጫና የጋራ ትግል መስኮች ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

. የኅብረቱ ደጋፊዎችም ሆኑ በኅብረቱ ያልተካተቱ ሌሎች የሀገራችን ዴሞክራቶች በሙሉ የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ከጎናቸው በማሰለፍ ከኢሕአዴግ መንግሥት ተላቀው ኢትዮጵያ ካለችበት የቀውስ አዙሪት ወጥታ የዴሞክራሲንና የልማት ጎዳና እንድትይዝ ያስችላል በሚል ጽኑ ዕምነት አማራጭ የጋራ ትግል ሰነድ አቅርበናል።

*ብሔራዊ ክብርና ሉአላዊነት የሚረጋገጡት በሕዝብ አንድነት ብቻ ነው!!!*
*ድል በኅብረት! ኅብረት ለጋራ ድል!!*

_____________ ይቀጥላል _____________